

# ወያኔ፣ የሳጥናኤል መታወቂያ የሆነውን ኣርማ ከሰንደቅ ኣላማችን ላይ መለጠፉን፣ መድህን ኣጥብቆ ያወግዛል፡፡

የኢትዮጵያችን ሰንደቅ ኣላማ በሶስት ህብረ ቀለማት ያሸበረቀች ሆና ለብዙ ዘመናት ኖራለች፡፡ እነኝህም ህብረ ቀለማት፣ ከላይ ኣረንጓዴ ቀለም ሲሆን፣ ትርጉሙም የሃገራችንን ብሩህ ተስፋ፣ የምድሯን ልምላሜና የተፈጥሮ ሃብት ፀጋ የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ ሁለተኛውና የመካከለኛው ኣካል ደግሞ ቀለሙ ቢጫ ሲሆን፣ የሃገራችንን ኣበባዎችና ፍራፍሬዎች ከማመልከቱም በላይ የተለያዩ ሃይማኖቶችን የሚከተሉ ኢትዮጵያውያን፣ ክርስቲያኑ፣ እስላሙና ኣይሁዳውያኑ በፍቅር ተሳስረው የሚኖሩባትን፣ በፈሪሃ እግዚኣብሄር የታነፀች ሃገራቸውን ኢትዮጵያን እንደገነቡ የሚገልፅ ነው፡፡ ሶስተኛው፣ ከቢጫው ግርጌ የሚገኘው ቀለም ደግሞ ቀይ ነው፡፡ ይኸኛው፣ ኢትዮጵያውያን እጅ ለእጅ ተያይዘው፣ ህይወታቸውን ሰውተው፣ ነፃነታቸውን እና ኣንድነታቸውን ለዘመናት መጠበቃቸውንና ማስከበራቸውን የሚገልፅ ነው፡፡

የመድህን ፓርቲ ኣርማ፣ በፓርቲው መተዳደርያ ደንብ ኣንቀፅ ሶስት መሰረት የኩራታችን፣ የተስፋችን፣ የነፃነታችን ምልክት በሆነችው ሰንደቅ ኣላማችን እንዲያሸበርቅ፣ የፓርቲያችንም ልዩ መልለያ እንዲሆን የተወሰነው ለዚህ ነው፡፡ የዚህም ኣርማ ትርጉም በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ እንደሚከተለው ተዘርዝሯል፡፡

የኢትዮጵያን ካርታ ያቀፈው የውስጥ ቀለበት፣ መላውን የኢትዮጵያን ህዝብ የምታቅፍ፣ የመላውን ህብረተሰብና ማህበረሰብ ክፍሎች እኩልነትና መብቶች የምታከብር፣ ያልተከፋፈለች እናት ኢትዮጵያን ያሳያል፡፡ ሁለተኛው ቀለበት የማይናወፀውን የህዝቧን ህብረት፣ ክንዳቸውን በኣንድነት ኣንስተው ሃገራቸውን የሚጠብቁትን ጀግኖች ኣርበኞቿን ያመለክታል፡፡ ዋርካው፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ስረ መሰረቱ ኣንድ መሆኑንና ተፈጥሮ ያስተማራቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ሁሉ ተመሳሳይ እድል እንደሚጠብቃቸው ያሳያል፡፡ ሶስተኛው የመድህን ኣርማ ቀለበት፣ ኢትዮጵያ የኣለም ማህረሰብ ኣካል ብቻ ሳትሆን ለሰው ልጅ ዘር ምንጩ መሆኗን የሚያሳይ ዋልታ ነው፡፡ በተጨማሪም፣ ከውጩ ቀለበት ኣድማስ ላይ የልማት የዲሞክራሲ የሰላምና የተስፋ ምልክት የሆነች ኣንፀባራቂ ፀሃይ ትታያለች፡፡ በመጨረሻም በኣርማው ስር መድህን የሚል ቃል ተፅፎበታል፡፡ ይህም፣ የኢትዮጵያ መድህን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ በፈጣሪ ኣምላክ ፈቃድና በኢትዮጵያ ህዝብ ድጋፍ በሃገሪቱ እኩልነት፣ እድገት ሰላምና ዲሞክራሲን ለማስፈን፣ የህዝቡን ኣንድነትና ደህንነት ለመጠበቅ ቆርጦ መነሳቱን የሚገልፅ ነው፡፡ የመድህን ፓርቲ ኣርማ ያጌጠውና ያሸበረቀው በእነዚህ ተስፋዎች፣ የኣንድነትና የነፃነት መግለጫችን በሆነችው ሰንደቅ ኣላማችን ነው፡፡

በኣንፃሩ ወያኔ «ህገ መንግስት» እያለ የሚጠራው ኣዋጅ፣ በቁጥር 1/1987 በኣንቀፅ ሶስት ስለሃገራችን ሰንደቅ ኣላማ የሚከተለውን ያትታል፡፡

> *የኢትዮጵያ ሰንደቅ ኣላማ ከላይ ኣረንጓዴ ከመሃል ቢጫ ከታች ቀይ ሆኖ በመሃሉ ብሄራዊ ኣርማ ይኖረዋል፡፡ ሶስቱም ቀለማት እኩል ሆነው በኣግድም ይቀመጣሉ፡፡ ብሄራዊ ኣርማ የኢትዮጵያ ብሄሮች ብሄረሰቦች ህዝቦች እና ሃይማኖቶች በእኩልነትና በኣንድነት ለመኖር ያላቸውን ተስፋ የሚያንፀባርቅ ይሆናል፡፡*

የመላው ኢትዮጵያውያን የነፃነት ኣርማና የእኛነታችን መግለጫ በሆነችው ሰንደቅ ኣላማችን መሃከል በወያኔ ትእዛዝ የሚለጠፈውና ወያኔም «ብሄራዊ» የሚለው ኣርማ፣ ኣምስት ጦሮች ያሉት በቀለበት የተከበበ ኮከብ ነው፡፡ ለመሆኑ ይህ የወያኔ ኣርማ ትርጉሙ ምንድን ነው?

በኣለም፣ በተለይም በኣውሮፓና በኣሜሪካ የሚኖሩ፣ በኣንድ ኣምላክ የማያመልኩ፣ ህይወታቸው፣ ኣኗኗራቸውና ድርጊታቸው ሁሉ በሃይማኖት ያልተገደበ፣ ታላላቅ የሃይማኖት መሪዎችን የሚያወግዙ፣ ቁጥራቸው በጣም ኣናሳ የሆኑ ወገኖች ኣሉ፡፡ እነዚህም ኣክራሪ የህብተሰብ ኣፈንጋጮች፣ ኣምልኮተ ሳጥናኤልን እንጅ ሌላ ሃይማኖት ኣይቀበሉም፡፡ እንዲያውም፣ ሃይማኖቶችን ሁሉ ያወግዛሉ፡፡ በምትኩም ሳጥናኤልን እንደፈጣሪያቸው ያመልካሉ፡፡ ወያኔ በኢትዮጵያ ሰንቅ ኣላማ ላይ እንዲለጠፍ የሚያዘንን ኣርማም የሃይማኖታቸው መግለጫ ኣድርገው ይጠቀሙበታል፡፡ ትርጉሙም እንደሚከተለው ነው፡፡ በክከቡ ወደላይ የሚታዩት ቀስቶች ጥንቆላ፣ መተትና ሳጥናኤልን ማምለክ ተቀባይነት እንዳለውና ከእንሰሳት ያልተለየ የግብረ ስጋ ግንኙነትን መፈፀም ኣግባብ መሆኑን ሲገልፁ ወደታች የሚያመለክቱት የኮከቡ ቀስቶች ደግሞ የሳጥናኤልን የኣለም ገዥነትና ታላቅነትን ያሳያሉ፡፡ (http://en.wikipedia.org/wiki/Satanism)

እንግዴህ፣ ወያኔ የሚለን፣ «ኢትዮጵያ ሳጥናኤልን እንጂ እግዚኣብሄርን የሚያመልኩ ሰዎች ሃገር ኣይደለችም» ነው፡፡ ስለዚህም ነው የወያኔ ኣገዛዝ ገና ከጅምሩ ኣብዮታዊ ዴሞክራሲ የተባለው፡፡ የዚህ ኣገዛዝ ስልት ተከታዮች ፈጣሪን በጠላትነት ይፈርጃሉ፡፡ «ሃይማኖትን መከተል፣ ኣእምሮንና መላ ሰውነትን የሚያደነዝዙ እፆችን እንደመውሰድ ነው» ብለውም ያስተምራሉ፡፡ ስለዚህ፣ የወያኔው መሪ ታላቁን ሳጥናኤላቸውን ቢያመልኩ ኣይገርምም፡፡ የሳጥናኤል ኣርማ ግን የኢትዮጵያውያን ኣርማ ሊሆን ኣይችልም፡፡ መድህን በፈሪሃ እግዚኣብሄር ኣምልኮ የተዋጠው ኢትዮጵያዊ ላይ በወያኔ የተጫነውን የሳጥናኤል ኣርማ እንዲሁም በህዝቡ ላይ ኣርማውን የጫኑበትን ኣምባ ገነኖች ያወግዛል፡፡ ኢትዮጵያውያን በሞላ ተቃውሞኣችንን እንደሚከተለው መግለፅ ግዴታችን ነው፡፡

1. *በሃዘናችን በደስታችን እንዲሁም በተለያዩ ብሄራዊ በኣሎቻችን የነፃነታችን ኣርማ የእኛነታችን መግለጫ የሆነችውን ሰንደቅ ኣላማችን ብቻ በቤታችንና በስራ ቦታችን ሁሉ ማውለብለብ ይኖርብናል፡፡*
2. *በምናደርጋቸው ባርኔጣዎች፣ በምንለብሳቸው ኮቶችም ሆነ ሸሚዞች ላይ ሰንደቅ ኣላማችንን ብቻ መለጠፍና በኩራት ማሳየት ተገቢ ነው፡፡*
3. *ኢትዮጵያውያን ሴቶች የወያኔን ኣርማ የማይቀበሉ መሆናቸውን በሚገልፁ ነጠላዎች፣ ሻሾችና ቀሚሶች ኣጊጠው የሳጥናኤል ወገኖች ኣለመሆናቸውን ለኣለም ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡*

ኢትዮጵያ የፈጣሪ እንጂ የሳጥናኤል ሃገር ያለመሆንኗን ወያኔም ሆነ የሌላው ኣለም ህዝብ እንዲረዳ ማድረግ የኢትዮጵያውያን ሁሉ ግዴታ ነው፡፡ የሃገራችን ለኣምባገነንነት፣ ለረሃብና እሮሮ መጋለጥ የባህላችን መረገጥና ለሳጥናኤል ኣምልኮት መመቻቸት መንስኤው ወያኔ ስለሆነ መላው ኢትዮጵያ ተባብሮ የወያኔን ፀረ ሃገር፣ ፀረ ህዝብ፣ ፀረ ታሪክና ፀረ ሃይማኖት ኣገዛዝ ጠራርጎ ኣስወግዶ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ይተካል፣ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ይገነባል፡፡

ኢትዮጵያ በቆራጥ ልጆቿ ትግል ነፃነቷን ትጎናፀፋለች፡፡ በዴሞክራሲ ኣሽብርቃም ለዘለኣለም ትኖራለች፡፡

**ኣባል ይሁኑ፥ http://www.medhin.org/member/support.htm**